አትወደድ:: ቢቻልህ አኗኗርህና መኝታህ ከምታፍረውና ከምታከብረው ሰው ጋር ይሁን:: ይህም ጓደኛህ ወይም ከቤተሰቦችህ አንዱ ሊሆን ይችላል:: ከብቸኝነት ይልቅ መወያየትን ይልቁንም መንፈሳዊ ውይይትን ዘወትር አድርግ:: በጸሎት ከሚረዱህ መንፈሳዊያን መምህራንና አባቶች ጋር ጊዜ ማሳለፍን ውደድ:: ከእነርሱ ጋር በመወያየትህ በጸሎታቸው እንዳይረሱህ ከማድረግ ጋር ለነፍስህ ወደብ የሚሆኑ ብዙ መንፈሳዊ ነገሮችን ትማራለህና::

ረ. እንቅልፍ የያዘህ ስለ መሰለህ ብቻ ወደ መኝታ አትሂድ:: በቂ ዕረፍት አግኝቼ የለምን? መኝታ ለምን አስፈለገኝ? ብለህ ራስህን ጠይቅ:: አንዳንድ ጊዜ ስትተኛ ውለህ እንቅልፍ ያምርሃልና:: ነገር ግን ሰይጣን ሊፈትንህ ከሆነ በምትተኛበት ጊዜ እንቅልፍ ከአይንህ ይርቃል:: ተከትሎም ፈተናው ይመጣና ወደ ዝሙት ሕሊናህ ይሳባል:: ሰውነትህንም በመደባበስ ፍትወትህን ለማርካት ትጥራለህ:: ስለዚህ ከመተኛትህ በፊት በደንብ መድከምህንና ቶሎ ማሸለብ መቻልህን መርምረህ ተኛ::

ሰ. ጸሎት ማድረግንም አትርሳ የሚረሳ ነገር አይደለምና:: ስትተኛም በጀርባህ ወይም በሆድህ አትተኛ:: ከዚህ ይልቅ በጎንህ ለመተኛት ሞክር:: አመጋገብህ በልክ ይሁን ጾምን በተገቢው መንገድ ጹም:: ቅዱሳት መጻሕፍትን አንብብ:: የመንፈሳዊ ሙያ ባለቤት ከሆንክ የምታውቀውን ዜማ ድምፅ አወጥተህ አንጎራጉር:: ያም ባይሆን የምትችለውን መዝሙር ዘምር::

ሸ. እንዲህ ያለ ፈተና ሲነሣብህ አንድ ዓይነት የአካል እንቅስቃሴ (ስፖርት) ሥራ:: ወይም ወዲህና ወዲያ ተንቀሣቀስ:: ከዚህም ሁሉ ይልቅ ደግሞ ከሆነልህ መስገድህ ይመረጣል:: ሽንትን መሽናትም ጥሩ መድኃኒት ሊሆንህ ይችላል:: በየጊዜው ጸበል





መጠመቅንም ቸል አትበል:: ነገር ግን ይህን በምታደርግበት ጊዜ ሕዋሳተ አንስትን ከማየት በእጅጉ ተጠንቀቅ:: "

ቀ. ሰውነትህ ሲበላህ ይልቁኑም ወደ አባለ ዘርዕ አካባቢ ከሆነ ትኩረት ሰጥተህ አታስበው:: ምክንያት እንዳይሆንብህ ተጣጥበህ ንጹሕ ለመሆን ሞክር:: የበላህን ቦታ ግን በምንም መልኩ አትከከው:: ማከክ ሰውነትን ከማቁሰል በቀር ይህን ለመሰለ ፈተና መፍትሔ አይሆንምና:: ከዚያ ይልቅ መጽሐፈ መነኮሳት «ግበር ትእምርተ መስቀል በሕሊናከ ውስተ መካነ ደዌከ» ፤ «ሕመም ወይም ማሳከክ በተሰማህ ቦታ ላይ በሕሊናህ የመስቀል ምልክት ሥራ» ይላልና:: በሚያሳክክህ ቦታ ላይ በሕሊናህ አማትብበት:: በሕሊናም ማለቱ የሚያይህ ሰው ነገር እንዳይመራመርኽ ለማድረግ ነው:: በተረፈ ግን አጥብቀህ ጸልይ:: ሁላችንንም እግዚአብሔር ይርዳን!

ኃጢአት ሲጸጸቱ ራስን መግደልም ተገቢ እንደ ሆነ ሳያሳምነን አይቀርም:: ራስን የማጥፋት ሓሳብ ብልትን ከመቁረጥ ይጀምራልና:: ማቴ27፥3-5፤ የሐዋ1፥16-20

በፍትወት መቃጠል የሚመነጨው ከውስጥ ነው:: ስለሆነም ውጫዊ ሕዋስ ኀፍረተ አካልን በመቁረጥ ከፍትወት መገላገል አይቻልም:: ሲራክ «ፈቃዱ ላይፈጸምለት ጃንደረባ ቆንጆ ይመኛል (ያቅፋል)» በማለት ተናግሯል:: ይህም ምንም ጃንደረባ (ስልብ) ቢሆኑ ፍትወት ከልብ አለመራቁን ያመለክታል:: አካልን ቆርጦ ፍትወትን እንዲራቁ ማሰብ ጠብ መንጃ ተኩሼ ሰይጣንን እገላለው እንደ ማለት ነው::

ሰይጣን አካልህን እስክትቆርጠው ድረስ በልዩ ልዩ መንገድ እያደፋፈረ ያነሣሣዛል:: እንደ ጀግናና ቁርጠኛ ሰው ለመታየት ብልታቸውን የሚቆርጡ አሉ:: ይህ በትዕቢትና በከንቱ ውዳሴ መሻት የተነሣ የሚመጣ ነው:: ሆኖም «ምትረተ እስኪት» ሁልጊዜ መጠን የሌለው ጸጸት ማስከተሉ አይቀርምና ከወዲሁ ማሰብ ብልህነት ነው:: ሰው የሚሠራው ኃጢአት ዝሙት ብቻ አይደለም:: ራሱን ቢመረምር ከዝሙትም የከፋ ኃጢአት ይገኝበታል:: ለወሬ ካልሆነ በቀር ከኃጢአት ነጻ ሊያወጣ የማይችልን አማራጭ መከተል ምን ይጠቅማል? ከማንኛውም ኃጢአት ለመለየት ኃጢአትን ከልብ መጥላትና እግዚአብሔርን መፍራት ያስፈልጋል:: እነዚህ ንስሐንና በጎ ሥራን ይወልዳሉና::

«ምትረተ እስኪት» ስሜታዊነትን፣ ሽንፈትን፣ ስንፍናን፣ ስልቹነትን፣ ታካችነትን፣ አርቆ አለማሰብን ያመለክታል:: ምክንያቱም በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደትና በመሳሰሉት መንፈሳዊ





ተግባራት እየታገሉ ከዝሙት ለመለየት ከመጣጣር ይልቅ በቅጽበት ለመገላገል ከመፈለግ የሚመነጭ ሐሳብ ስለሆነ ነው:: የሚያስከትለውን የጤና ቀውስ፣ ጸጸትና እስከ ሞት የሚያደርስ ሥቃይን ከዚህ በተጨማሪም ከእግዚአብሔር ሕግ አንጻር ተቀባይነት እንደ ሌለው አለማወቅ አርቆ አለማሰብ መሆኑንም ያስረዳል::

ፍትሐ ነገሥት (ፍትሐ መንፈሳዊ) ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ራሳቸውን ጃንደረቦች ያደረጉ አሉ» በማለት በወንጌል የተናገረውን ቃል ሲያብራራ «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ቃል አባለ ዘርን ስለመቁረጥ አልተናገረውም እንዲህ ያለ ሥራ ከመንግሥተ ሰማይ ያርቃልና» ይላል:: ከዚህም በተጨማሪ «ኀፍረተ አካሉን የቆረጠ ሰው ካህን ቢሆን ይሻር» ይላል:: ካህን ካልሆነ ደግሞ ክህነት እንዳይሰጠው ያግዳል:: በሕገ ኦሪት ደግሞ ብልቱ የተቆረጠ ሰው ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ እንዳይገባ ይከለከል ነበር:: ዘዳ23፥1

ያለውድ በግድ፣ በጦርነትና በልዩ ልዩ ደዌ ምክንያት አባለ ዘራቸው የተቆረጠ ሰዎች ከላይ የተጠቀሰው እገዳ አይመለከታቸውም:: ማለትም ክህነት መቀበልና በክህነታቸው መቀጠል ይችላሉ::

ይህን መንፈሳዊ አስተምህሮ ከመገንዘብ አስቀድሞ እስኪታቸውን ለቆረጡ ሰዎች ሌሎች ሰዎች ሊያደርጉላቸው ስለሚገባው ነገር መጽሐፈ መነኮሳት «ኢታስተኀቅርዎሙ ወኢትመንኖሙ ለምቱራን አባል» ይላል:: «አካል ብልት የጎደላቸውን ሰዎች አታዋርዷቸው» ማለት ነው:: ምክንያቱም ምንም ስሕተት ቢሆን አንድ ጊዜ ፈጽመውታል:: በተጨማሪም ከማወቃቸው በፊት

በላይ ምን ሥሪ፣ ሊመጣለት ይችላል? ውበት ሥራ እንጂ መልክ መሆን የለበትም። ስለዚህ የጡት ውበቱ ልጆችን ማሳደጉ ነው!

ሌላው ሴቶች ለዐቅመ ሔዋን መድረሳቸውን የሚያበስር ዋነኛ ምልክት የወር አበባ መታየት መጀመሩ ነው። ስለ ወር አበባ አሰያየም፣ ምንነትና ተያያዥ ሥርዓቶች ከዚህ በታች ራሱን ችሎ በተብራራ መልኩ ተጽፏል።





# ምዕራፍ ሰባት

## የወር አበባ

<u>አሰያየሙ</u>:-

ሀ. በመንፈሳዊያን መጻሕፍት የወር አበባ ልዩ ልዩ ስያሜዎች አሉት። ሊቀ ነቢያት ሙሴ ስለ አብርሃምና ስለ ሚስቱ ሕይወት በሚተርክበት ጊዜ «አብርሃምና ሣራም በዕድሜያቸው ሸምግለው ፈጽመው አርጅተው ነበር፤ በሴቶችም የሚሆነው ልማድ ከሣራ ተቋርጦ ነበር» በማለት ተናግሯል። በዚህም ትረካው ነቢዩ ሙሴ የወር አበባን «በሴቶች የሚሆነው ልማድ» በማለት ለመጀመሪያ ጊዜ ሰይሞታል። ዘፍ18፥11 ከዚህ የሊቀ ነቢያት ሙሴ አሰያየም በመነሣት ሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍትና መምህራነ ቤተ ክርስቲያን የወር አበባ ለማለት «ልማደ አንስት» ሲሉ ይገኛሉ።

ለ. ከእናታችን ከሣራ በኋላ ዘግይታ የተነሣችው የያዕቆብ ሚስት ራሔል ደግሞ «ልማደ አንስት»ን በሌላ ስፍራ በ«ሴቶች የሚደረስ ግዳጅ» ብላ ስትጠራው እናነባለን። ዘፍ31፥35 ከዚህም በመነሣት መንፈሳዊያን መጻሕፍት «ለወር አበባ ነዕታ ነበር» ለማለት «ከግዳጅዋ ጠርታ ነበር» ይላሉ። በዚህ ዘመን የሴቶች ግዳጅ በብዙኃን ዘንድ ተለይቶ የሚታወቀው «የወር አበባ» በመባል ነው።

ሐ. የወር አበባ የ«ወር» የተባለበት ምክንያት በየወሩ የሚታይ ስለ ሆነ በመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ አያስፈልገውም። «አበባ» የተባለበት ምክንያት ግን ሴቶች ልጆች ራሳቸው በዕፅ፣ በየወሩ የሚያዩት ደም በአበባው፣ የሚወልዷቸው ልጆች ደግሞ በፍሬው ስለሚመሰሉ ነው።

እናቶች ለልጆቻቸው ስለ ወር አበባ አስቀድመው በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: ይህን የሕይወት ጎዳና ያለፉበት በመሆኑ እናቶች ይመረጡ እንጂ አባቶችም ይህን በመሰለ ነገር ላይ ራሳቸውን ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል:: ይህን ካደረጉ ልጆቻቸውን ከመደንገጥ፣ ከመረበሽና ከመሳሰሉት ነገሮች ሊያድኗቸው ይችላሉ::

ልጆችም ይህን በመሰለ ጉዳይ ላይ ከማንኛውም ሰው ይልቅ ወላጆች እንደሚረዷቸው ዐውቀው በግልፅ ወላጆቻቸውን ማማከር ይኖርባቸዋል:: ራሔል «በሴቶች የሚደርስ ግዳጅ ደርሶብኛል» በማለት ለአባቷ ለላባ ስትነግረው ምንም እንዳላስፈራትና እንዳላሳፈራት ሁሉ ልጆችም ስለ ጉዳዩ በቂ ግንዛቤ ባይኖራቸው እንኳን «ይህ ነገር ምንድር ነው?» በማለት ስለ ወር አበባ ወላጆቻቸውን ሳይፈሩ በግልጽ ቢያማክሩ መልካም ነው:: ዘፍ31፥35

ወጣት ሴቶች የወር አበባን በተመለከተ የሚሰጡትን መንፈሳዊ ትምህርቶች መከታተል፣ አበው መምህራንን መጠየቅና ከዚህ ጋር ተያይዘው የተሠሩትን የቤተክርስቲያን ሥርዓቶችን በሚገባ ማወቅ ይኖርባቸዋል:: በተጨማሪ የወር አበባን በተመለከተ ምርቱን ከግርድ እየለዩ ለተመለከታቸው የሥነ ሕይወትና የሥነ ተዋልዶ መጻሕፍት መጠነኛ ጠቀሜታ አላቸው::

እመቤታችን ድንግል ማርያም በስእለት ተሰጥታ በቤተ መቅደስ እየኖረች ሳለ ለዐቅመ ሔዋን ስትደርስ አይሁድ እንደ ሌሎች ሴቶች አይተዋት ቤተመቅደሳችንን በልማደ አንስት ታሳድፍብናለች ብለው አስወጥተዋታል:: ይሁን እንጂ ከእናቷ ማኅፀን ጀምራ በመንፈስ ቅዱስ የተጠበቀች እመቤታችን ግን በዚህ ዓለም ለ64 ዓመታት ስትኖር ልማደ አንስት አላገኛትም:: ከእርሷ በቀር ግን





ልማደ አንስት ሳያገኛት ዓቅመ ሔዋንን የምታልፍ ጤናማ ሴት የለችም፣ አትኖርምም::

## የወር አበባ መቼት

«መቼት» ማለት መቼና የት ማለት ነው:: የወር አበባ መቼት አለው:: መቼቱ አዳምና ሔዋን በኃጢአት ከወደቁ በኋላ ከገነት ውጭ ነው:: አዳምና ሔዋን በገነት በነበሩበት ጊዜ ምንም እንኳን በሔዋን ባሕርይ ደመ ጽጌ የነበረ ቢሆንም ደሟ በአፍአ አታይም ነበር::

ዕፀ በለስን በልተው አዳምና ሔዋን ፈጣሪያቸውን በበደሉ ጊዜ ግን ሔዋን ደመ ዕፅ በለስን አፍስሳለችና «ወበከመ አድመውኪያ ለእንተኩ ዕፅ ከማሁ ድምዊ ለለወርኅ» በማለት ደሟ በየወሩ እንዲፈስ ፈጣሪ ፈረደባት:: ስለዚህ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሔዋን ከገነት ውጭ ሆና ስትኖር ደሟ በየወሩ ይፈስ ጀመር::

እንደሚታወቀው ዝናብ መዝነብ የጀመረው በምድር ላይ ኃጢአት እየበዛ መጥቶ እግዚአብሔር ዓለምን በጥፋት ውኃ እንድትጠፋ ካደረገ በኋላ ነው:: ከዚያ አስቀድሞ ውስጥ ለውስጥ በሚሄድ ጉም ምድር ትረሰርስ ነበር እንጂ ዝናብ አይዘንብም ነበር:: ከጥፋት ውኃ በኋላ ግን ጌታ እግዚአብሔር ክረምትና በጋን ለማፈራረቅ ለኖህ በገባለት ቃል ኪዳን መሠረት ዝናብ መዝነብ ጀመረ:: ዘፍ8፥22

ከዚህ በኋላ ውስጥ ለውስጥ ያረካት የነበረው ውኃ ዝናብ ሆኖ እየመጣ ምድርን ከውጭ ያጨቀያት ጀመር:: ምድር ለሔዋን ምሳሌ ናት ሰው ምድር ይባላልና:: «እስመ አንተ ምድር፣ ዘምድረ ለብሰ» የሚሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊና መንፈሳዊ ጥቅሶች ሰው ምድር ለመባል ምስክሮች ናቸው:: ዝናብ ደግሞ የወር አበባ ምሳሌ ነው:: ከውስጥ

ለውስጥ ይሄድ የነበረው ውኃ ከጊዜ በኋላ በውጭ ተገልጦ ምድርን ማጨቅየቱ በሔዋን ባሕርይ የነበረ ደም ከጊዜ በኋላ በአፍአ መታየት መጀመሩን ያስረዳል።

በዚህ ምስጢር መሠረት ሔዋን የወር አበባ ማየት የጀመረችው ከገነት ውጭ ነው። ጊዜውም አዳምና ሔዋን የፈጣሪን ትዕዛዝ ተላልፈው ከገነት ከተባረሩ በኋላ መሆኑ ግልጽ ነው።

## በወር አበባ ወቅት የሚያጋጥም የሕመም ስሜት

ለዐቅመ ሔዋን የደረሰች ሴት ደመ ፅጌ በምታይባቸው ዕለታት የጡንቻና የአጥንት መልፈስፈስ (ድካም) ያጋጥማታል። በተጨማሪም የጀርባ ወይም የወገብ ሕመም ሆድ ቁርጠት፣ የምግብ መንሸራሸር ችግርና የምግብ ፍላጐት ማጣት ለመሳሰሉት የሕመም ስሜቶች ስለምትጋለጥ በአመጋገብና በቂ ዕረፍት በማግኘት ረገድ ምቾት ያስፈልጋታል።

በቂ ዕረፍት ማለት ተኝቶ መዋል ማለት አይደለም። በወር አበባ ወቅት የሚኖረውን የሕመም ስሜት ለመቀነስ በቂ ዕረፍት ማግኘት እንደተጠበቀ ሆኖ ቀልጣፋ የተግባርና የእንቅስቃሴ ሰው ሆኖ መገኘት እንደሚያስፈልግ ባለሙያዎች ይስማማሉ።

ከሚኖረው የሕመም ስሜት በተጨማሪ ትዝብት ላይ እስከ መውደቅ የሚያደርስ መቅበጥበጥና አንዳንድ ጊዜም የመደበር (መደበትና) በሆነው ባልሆነው በቀላሉ የመከፋት ሁኔታ ሊንጸባረቅ ይችላል።





ከላይ የተጠቀሱትን የሕመም ስሜቶችንና በጠባይ ላይ የሚከሰቱትን ለውጦች መረዳት በወር አበባ ላይ የሚገኙትን ሴቶች በሚገባ ለመንከባከብ ይረዳል። በዚህ ወቅት የሚገኙ ሴቶችን መንከባከብ እንደሚገባ ከቀደሙት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮች መረዳት ይቻላል።

ላባ የተባለ ሰው የጠፋበትን ዕቃ በሚፈልግበት ጊዜ በወር አበባ ላይ ትገኝ የነበረችውን ልጁን ራሔልን ከተቀመጠችበት ቦታ ላለማስነሣት የተቀመጠችበትን ስፍራ ከመበርበር ተቆጥቧል። በምን አውቆ ቢባል እርሷም አባትዋን «በፊትህ ለመቆም ስላልቻልኩ አትቆጣብኝ በሴቶች የሚደርስ ግዳጅ ደርሶብኛል» አለችው ስለሚል ከዚህ የይቅር በለኝ ቃሏ ያለችበትን ሁኔታ ለመገንዘብ ችሎ ነበር። ዘፍ31፥35 ይህ የላባ ታሪክ በወር አበባ ላይ ለሚገኙ ሴቶች ሌሎች ሰዎች ሁሉ ማድረግ ያለባቸውን እንክብካቤ በግልጽ ያስረዳል።

## የወር አበባ «ርኩሰት» ነውን?

ምንጩ ባይታቅም በወር አበባ ላይ ያሉ አንዳንድ ሴቶች መስቀል ሊያሳልሟቸው ሲሉ «ርኩስ ነኝ አያሳልሙኝ!» ሲሉ ይደመጣሉ። ሌሎች ደግሞ ደመ ፅጌ ሲታያቸው ከጸሎት፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከማንበብ፣ አልፎ ተርፎም ለዝክርና ለጸዲቅ የሚሆን ማንኛውንም ሥራ ከመሥራት ይከለከላሉ። ማለትም ስንዴ ከመልቀም፣ አሻሮ ከመቁላት፣ እንኩሮ ከማኮር እስከ መከልከል ይደርሳሉ። በእርግጥ የወር አበባ ርኩሰት ነውን? ርኩስስ ያሰኛልን?

በእርግጥ በዘመነ ኦሪት የወር አበባ የርኩሰትና የመርገም ምልክት ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ በዘመነ ኦሪት የወር አበባ የምታይን ሴት ለመጥቀስ «በመርገምዋ ርኩሰት ሳለች» እና «ባለ መርገም ሴት» ሲል ይገኛል። ዘሌ.18፥19፤ 20፥18 ከወር አበባ የነጻችን ሴት

ለመጥቀስ ደግሞ «ክርኩሰትዋ ነጽታ» ነበርና በማለት ይገልጻል። 1ሳሙ11፥4 እነዚህ ጥቅሶች በሙሉ የወር አበባ በዘመነ ኦሪት የመርገምና የርኩሰት ምልክት ነበር ያልነውን ለማጉላት በዋቢነት የማጠቀሱ ናቸው።

ይህ የሆነበት ምክንያት የወር አበባ የተከሰተው ሔዋን ደመ ዕፀ በለስን በማፍሰሷ ምክንያት እግዚአብሔር «ወበከመ አድመውኪዮ ለዛቲ ዕፅ ከማሁ ድምዊ ለለወርኀ» ብሎ ከረገማት በኋላ በመከሠቱ ነው። ትርጓሜውም «የዚህችን ዕፀ በለስ ደሟን እንዳፈሰሽ የአንቺም ደም በየወሩ ይፍሰስ» ማለት ነው።

ይሁን እንጂ የረከሰ በተቀደሰበት የተረገመ በተባረከበት በዚህ በአዲስ ኪዳን ዘመን የወር አበባን ርኩሰት ነው ማለት ቀርቶ መታሰብም የለበትም። የወር አበባ ርኩሰት መሆኑ ቀርቷል። ርኩሰት አይደለም፣ ርኩስም አያሰኝም። እኛ ባለንበት በዚህ በአዲስ ኪዳን ዘመን የወር አበባን ርኩሰት ነው ማለት ከባድ ኃጢአት ከመሆንም አልፎ ክህደት ይባላል። በአዲስ ኪዳን ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በፈጸመው ቤዛነት መርገምነቱና ርኩሰትነቱ ተወግዷልና።

አንድ መዘንጋት የሌለበት ነገር የወር አበባ ርኩሰት ባይሆንም አደፍ ነው። አደፍ (እዳሪ) ነው ማለትና ርኩሰት ነው ማለት ከፍተኛ ልዩነት አላቸው። ርኩሰት ውሳጣዊ ነው፤ በንስሐ እንጂ በውኃ አይጠራም። አደፍ ግን አፍአዊና በግዘፍ የሚታይ ነው። ስለዚህ ውኃ ያጠራዋል። እንደዚህም ሁሉ የወር አበባ አደፍ (እዳሪ) ነው ሲባል ሰውነታችን እንደሚያስወግዳቸው ማንኛውም ሌሎች ነገሮች አፍአዊ ቆሻሻ ነው ማለት ነው።"

የወር አበባ በሴቶች ባሕርይ ሳለ እንደ ቆሻሻ አይቆጠርም። ሰውነት ሲያስወግደው ግን ይቆጠራል። ለምሳሌ፦ ዛሕል (ንፍጥ)፣





ሽንት፣ ምራቅ፣ ዓይነ ምድር (እዳሪ)፣ ላብ እነዚህ ሁሉ በሰው ባሕርይ በሰውነት ውስጥ ሳሉ ጠቃሚና አስፈላጊ ነበሩ። ሰውነት ሲያስወግዳቸው ግን እንደ ጉድፍ ይቆጠራሉ። የወር አበባም እንዲሁ ነው። ዛሕል (ንፍጥ) ካፍንጫ ከወጣ እዳሪ ነው። ርኩሰት ግን አይደለም የወር አበባም እንዲሁ ነው።

የወር አበባ ርኩሰት ባለመሆኑ መስቀል ከመሳም፣ ከመጸለይ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከማንበብና ከመድገም አያግድም። ያግዳል እንጂ የሚል ካለ አቡነ ዘበሰማያትን ጨምሮ ሰላም ለኪንና ሌሎች የጸሎት ዓይነቶችን በቃላቸው የሚነዱ ምዕመናት በብዙ ቁጥር ይገኛሉ። በወር አበባ ወቅት ቅዱሳት መጽሕፍትን ለማንበብ ከተከለከሉ በቃላቸው የያዙትን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ምን ሊያደርጉት ነው? ደግሞም ወረቀቱንና ብራናውን የሚያከብረው ቅዱስ ቃሉ አይደለምን? ቅዱሱን ቃል በልቡናቸው ይዘው ሳለ መጽሐፉን አትንኩት አታንቡት ማለት ግብዝነት አይሆንምን? የትኛው ይበልጣል? ወረቀቱና ብራናው ነውን? ወይስ ወረቀቱንና ብራናውን የሚያከብረው ቅዱስ ቃሉ? ብራናውንና ወረቀቱን እንዳይነኩና እንዳያነቡ የሚከለከሉ ከሆነ ቅዱስ ቃሉንም በቃላቸው እንዳይዙና እንዳያጠኑ መከልከል በተገባቸው ነበር። ከተፈቀደላቸው ግን መጻሕፍቱን ከማንበብና ከመድገም የሚከለክላቸው ማን ነው? ስለዚህ በወር አበባ ላይ የሚገኙ ሴቶች እነዚህን ተግባራት ከማከናወናን አይከለከሉም።

ከላይ የተጠቀሰውን ሐሳብ ከዚህ በታች የሰፈረው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ንጽጽራዊ በሆነ መንገድ ሲያጠናክረው እናገኘዋለን። «እናንተ፦ ማንም በቤተ መቅደስ የሚምል ምንም የለበትም ማንም በቤተ መቅደስ ወርቅ የሚምል ግን በመሐላው ይያዛል የምትሉ ዕውሮች መሪዎች ወዮላችሁ። እናንተ ደንቆሮዎችና ዕውሮች ማናቸው ይበልጣል? ወርቁ ነውን? ወይስ ወርቁን የቀደሰው ቤተ

መቅደስ? ደግሞችሁም፡- ማንም በመሠዊያው የሚምል ምንም የለበትም ማንም በላዩ ባለው መባ የሚምል ግን በመሐላው ይያዛል ትላላችሁ። እናንተ ደንቆሮዎችና ዕውሮች ማናቸው ይበልጣል? መባው ነውን? ወይስ መባውን የሚቀድሰው መሠዊያው? እንግዲህ በመሠዊያው የሚምለው በእርሱና በእርሱ ላይ ባለው ሁሉ ይምላል። በቤተ መቅደስም የሚምለው በእርሱና በእርሱ ላይ በሚኖረው ይምላል። በሰማይም የሚምለው በእግዚአብሔር ዙፋንና በእርሱ ላይ በተቀመጠው ይምላል።» ማቴ 23፥16-22

## በወር አበባ ወቅት መከልከል የሚገባው ከምን ከምን ነው?

ሴቶች ደመ ፅጌን በሚያዩበት ወቅት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አራት ዋና ዋና ነገሮች እንዳይፈጸሙ በመንፈሳዊ ሕግ ተከልክለዋል። እነዚህ ነገሮች ለምን እንደተከለከሉና ለመከልከላቸውም የሚቀርቡ መጽሐፍዊ መረጃዎች ተያይዘው ቀርበዋል።

### 1. ከሩካቤ

የወር አበባን የምታይ ሴት ባለትዳር ከሆነች በደሟ ወቅት ምንም እንኳን ባሏ ቢሆንም ሩካቤ መፈጸም በመንፈሳዊ ሕግ አይፈቀድላትም። የሕክምና ባለሙያዎችም ቢሆኑ በደም ወራት የሚደረግ ሩካቤ በአብዛኛው ለአባለ ዘር፣ ለልዩ ልዩ ተላላፊ በሽታዎችና እንዲሁም ለልክፈት (ለኢንፌክሽን) በቀላሉ ለመጋለጥ ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር ይናገራሉ።

በመንፈሳዊ አስተምህሮ ስንመለከተው ደግሞ የሰው ልጅ ዘር ክቡር ነው። ስለዚህ ሴት ልጅ በትክት (በወር አበባ) ላይ እያለች





ሩካቤን መፈጸም ክቡር ዘርን እዳሪ ከሆነ ደም ጋር ማዋሐድ ነውና ከባድ ኃጢአት ሆኖ ይቆጣራል።

መጽሐፍ ቅዱስ ሴት ልጅ ከግዳጅዋ ሳትነፃ የሚፈጸም ሩካቤን ሲከለክል እንዲህ ይላል፡- «እርሷም በመርገምዋ ርኩሰት ሳለች ኀፍረተ ሥጋዋን ትገልጽ ዘንድ ወደ ሴት አትቅረብ።» ዘሌ 18፥19 ይህንን ሕግ ተላልፎ ኀጢአት የሠራ ሰው ስለሚገባው ቅጣት ሲናገር ደግሞ፡- «ማንኛውም ሰው ከባለመርገም ሴት ጋር ቢተኛ ኀፍረተ ሥጋዋንም ቢገልጥ እርሷም የደሟን ፈሳሽ ገልጣለችና ሁለቱም ከሕዝባቸው መካከል ተለይተው ይጥፉ።» ይላል። ዘሌ20፥18

ትክቶ (የወር አበባ) ምንም' እንኳን በአዲስ ኪዳን መርገም ወይም ርኩሰት ስላልሆነ በዚህ ወቅት ሩካቤ የሚፈጽሙ ሰዎች እንደ ኦሪቱ ዘመን በድንጋይ ተወግረውና በእሳት ተቃጥለው እንዲጠፉ ባይደረግም ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን በመተላለፋቸው በመንፈሳዊ ቅጣት (በቀኖና) መቀጣታቸው አይቀርም። ምክንያቱም በወር አበባ ወቅት የሚፈጸም ሩካቤ በአዲስ ኪዳንም ክልክል ስለሆነ ነው። የወር አበባን ጨምሮ ባልና ሚስት ሩካቤ ከመፈጸም የሚታቀቡባቸው ወቅቶችና ዕለታት በ«ትዳርና ተላጽቆ» መጽሐፍ በምዕራፍ ስምንት ላይ በሚገባ ተዘርዝረዋልና ያን ይመልከቱ።

### 2. ከመጠመቅ

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ «ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ... የሰውነትን እድፍ ማስወገድ አይደለም። ለእግዚአብሔር የበጎ ሕሊና ልመና ነው እንጂ» በማለት ተናግሯል። 1ጴጥ3፥21 ስለዚህ ጥምቀት ሥጋዊ እድፍን ማስወገጃ ስላልሆነ ከመጠመቅ በፊት ተጣጥበው ከአፍአዊ እድፍ ከጠሩ በኋላ መጠመቅ ይገባል እንጂ

ከእድፍ ጋር ለመጠመቅ መቅረብ ተገቢ አይደለም:: ምክንያቱም የሥጋ ንጽሕና ለነፍስ ንጽሕናና ለንስሐ የመዘጋጀት ምልክት (ምሳሌ) ነውና::

እንዲህ ከሆነ የወር አበባ ከላይ እንደተገለጸው አደፍ ይባላልና በወር አበባ ላይ ሳሉ መጠመቅ ክልክል ነው:: ፍትሐ ነገሥት መንፈሳዊ «ወለእመ ተዳደቃ ወረከባ ለብእሲት ደመ ትክቶ ትጽናሕ እስከ ትነጽሕ» ማለትም «በመትጠመቀው ሴት በምትጠመቅበት ቀን አደፍ ቢመጣባት እስክትነፃ ድረስ ትቆይ» በማለት በወር አበባ ወቅት የሚደረግ ጥምቀትን ይከለክላል::.

በእርግጥ ከላይ የሰፈረው የፍትሐ ነገሥት ጥቅስ የሚመለከተው ለዓቅመ ሔዋን ከደረሱ በኋላ ክርስትና ለመነሣት የሚመጡ የንዑሰ ክርስቲያንን ጥምቀተ ክርስትና ነው:: ቢሆንም ይኸው ራሱ ጥቅስ ማንኛውም ክርስቲያን ከበሽታ ለመፈወስም ሆነ ለበረከት በየጊዜው ለሚጠመቀው የፈውስ ጥምቀት ሊጠቀስ ይችላል:: ምክንያቱም በወር አበባ ወቅት መጠመቅ የተከለከለበት ምክንያት ለየትኛውም የጥምቀት ዓይነት ቢሆን ምስጥሩ ያው በመሆኑ ነው::

አንዳንድ ጊዜ በጠና የታመሙ ሰዎች በጸበል ለመፈወስ ክትትል ሲጀምሩ ልዮ ልዩ ፈተና ያጋጥማቸዋል:: ከፈተናዎቻቸውም ውስጥ አንዱና ዋነኛው ሴቶች ከሆኑ በየወሩ ይታያቸው የነበረው የወር አበባ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ያለማቋረጥ ወይም በተደጋጋሚ መከሠቱ ነው::

ይህን የመሰለ ፈተና ሲከሰት ከሰይጣን ጋር እልክ መጋባትና ዝም ብዬ ብጠመቅ ምን አለበት? ማለት ሞኝነት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ «ክፋን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ» ይላልና ሥርዓት እየጣሱ ሰይጣንን ለመርታት አለመሞከር ጥሩ ነው::





ሮሜ12፥21 ሰይጣን ጸበል በመጠበቅ ብቻ ሳይሆን ሥርዓት በማክበርና በመታዘዝም ይሸነፋል:: «ያለኝ ዕድል መጠመቅ ብቻ ነው» ማለት ያለ ጸበል ሰይጣን የሚረታበት ነገር የለም ያሰኛል::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆች ሁሉ ባለጋራ የሆነ ዲያብሎስ በምን በምን ድል እንደሚሆን ባስተማረ ጊዜ በመጀመሪያ ከልብ ጋር የተስማማ እምነት እንደሚያስፈልግ ገልጿል:: በማስከተልም «ይህ ዓይነት ግን ከጸሎትና ከጾም በቀር አይወጣም» በማለት አብሮ አደግ ሰይጣንን አሳፍሮ ለማባረር ጾምና ጸሎት ዓይነተኛ መሣሪያዎች መሆናቸውን ጠቁሟል:: ማቴ17፥21 ስለዚህ ጸበል ለመጠመቅ የነበረን ዕድል በዚህ መልኩ ፈተና ሲገጥመው ተስፋ ሳይቆርጡ በጾም፣ በጸሎትና በመሳሰሉት መንፈሳዊ አማራጮች በመታገዥ ባለጋራን ድል ማድረግ ይቻላል::

በሌላ አቅጣጫ ወሳኙ እምነት በመሆኑ ካልተጠመቅሁ አይሆንም ከማለት ይልቅ በሕመም ምክንያት መጾምና ቆሞ መጸለይ ባይቻል እንኳን በጸበሉ መተሻሸትና መጠጣት ከመጠመቅ እኩል ነው:: መተሻሸትና መጠጣት እንዴት ይቻላል? እንዳይባል እድፍን ማጥራት እንዳይሆን በሚል መጠመቅ ተከለከለ እንጂ መጠጣት አልተከለከለም::

ከላይ የተጠቀሱትን አማራጭ መንገዶች መጠቀም ያልተቻላቸው ደካሞችና ሕመምተኞች እንደ ልቡናቸው የእምነት ደረጃ ለመጓዝ እንዲችሉ መምህራነ ቤተ ክርስቲያንን ማዋየትና በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን መመራት ይኖርባቸዋል::

ካህናተ ቤተ ክርስቲያን በዚህ መልኩ የሚቸገሩን እናቶችና እኅቶች እንዲጠመቁ በመፍቀድም ሆነ ሌሎች አማራጮችን በማመቻቸት ሊረዷቸው ይችላሉ:: መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት

የተሰኘ መጽሐፍ «ይቁረብ አይቁረብ» በሚል አርዕስት ሥር ባቀረበው ሐተታ «ከደመ ጽጌዋ ያልነፃች ሴት ከታመመች ለሥጋ ወደሙ አጋፋሪ የለውምና ትቁረብ» በማለት የግል አስተያየቱን ይሰጣል። ይህ አስተያየት ፅኑት ያለው (ችግር ያለበት፣ ሊቀበሉት የማይገባና ግትር) ነው። ምክንያቱም ሥጋ ወደሙ አጋፋሪ የለውም አይባልም። መላእክት፣ ካህናትና እያንዳንዱ ምእመን የሥጋ ወደሙ አጋፋሪዎች ናቸውና። ማለትም ማንም በማይገባ መንገድ ሥጋ ወደሙን እንዳይቀበል ይቆጣጠራሉ። ሆኖም ከላይ እንደተጠቀሰው አንዳንዶች ደፍረው ከደመ ጽጌ ያልነጹ ሴቶችን ቢታመሙ ይቁረቡ እስከ ማለት ድረስ ፈቃድ ከሰጡ እንዲጠመቁ መፍቀድ ለካህናት ቀላል ተግባር መሆኑን ያመለክታል።

ይኸው መጽሐፍ «ይሁን እንጂ ለሞት የምታሰጋ ብትሆን ነው እንጂ የማታሰጋ ከሆነ የቤተ ክርስቲያን ሕግ በሚያዘው መሠረት ወደ ቤተ ክርስቲያን አትገባም» በማለት አስተያየቱን ይደመድማል። ስለዚህ ይህን የመሰለ ፈቃድ በጸና ለታመሙ እንጂ ውለው አድረው ለመጠመቅ ፋታ ላላቸው ሁሉ አለ መሆኑን ልብ ማለት ይገባል።

## 3. ከመቁረብ

ምንም እንኳን ለቁርባን የሚያስፈልገውን ቅድመ ዝግጅት ያጠናቀቁ ቢሆኑም ሴቶች ከደመ ፅጌ ሳይነጹ ሥጋ ወደሙ መቀበል አይችሉም። ይህን ሥርዓት ተላልፎ ሴቶችን ከወር አበባ ሳይነጹ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲገቡና ሥጋውና ደሙን እንዲቀበሉ ያደረገ ቢኖር ዲያቆንም ሆነ ቄስ ከክህነቱ እንዲሻር ፍትሐ ነገሥት እንዲህ ሲል ይደነግጋል። «ወለእመ ተዓደወ ፩ሂ እምቀሳውስት ወዲያቆናት ወአብእ ብእሲተ ትክተ ኀበ ቤተ ክርስቲያን ወመጠዋ ቁርባነ በመዋዕለ ትክቶሃ ይደቅ እመዓርጊሁ» ይህ ዐረፍተ ነገር «ከግዳጅዋ ያልነጻችውን





ሴት በደሟ ወራት ከቤተ ክርስቲያን አግብቶ ሥጋውን ደሙን ያቀበላት ከመዓርጉ ይሻር» ማለት ነው። ፍት.ነገ.6 ዘሌ7፥19-21 ስለዚህ ሴቶች ከወር አበባ ሳይነጹ ሥጋውንና ደሙን መቀበል አይኖርባቸውም።

ይህን በተመለከተ የመጽሐፉ አስደናቂ አገላለጽ ደግሞ «እቴጌም ብትሆን» ማለቱ ነው። «እቴጌም ብትሆን» ማለት የንጉሥ ወይም የንግሥት እናት ወይም ራሷ ንግሥት ብትሆንም እንኳን ከደሟ ሳትነጻ ሥጋውና ደሙን ልትቀበል አትችልም ማለት ነው። አገላለጹ ሥርዓቱ ጽኑ መሆኑን ያስረዳል። ስለዚህ ሥጋ ወደሙን መቀበል የጓጓንበት ታላቅ በዓል ቢኖር፣ ሰርግ ወይም ሌላ ታላቅ ጉዳይ ቢኖርብንም በምንም አመካኝተን ቢሆን በወር አበባ ላይ ሳለን መቁረብ (ሥጋውንና ደሙን መቀበል) አንችልም። ከማንኛውም የኛ ጉዳይ ስለ ሥጋ ወደሙ የተሠራው ሥርዓት ይበልጣልና። ስለዚህ በቁርባን የሚጋቡ ሰዎች የሰርግ ቀናቸውን ከመወሰናቸውና የሰርግ ዝግጅት ከመጀመራቸው በፊት የሴቷን የወር አበባ ዑደት ለይቶ ማወቅና ከሰርግ ቀኗ ጋር አንድ እንዳይሆን መጠንቀቅ አለባቸው። ስለምን ቢባል በወር አበባ ላይ ያለች ሴት በምንም ዓይነት ማስተዛዘኛ ለመቁረብ ስለማይፈቀድላት ነው።

## 4. ቤተ መቅደስ ከመግባት

ሴት ልጅ መዋዕለ ንጽሕናዋን ሳትፈጽም በደመ ጽጌዋ ሳለች ወደ ቤተመቅደስ እንዳትገባ ሥርዓት ተሠርቷል። ከግዳጅዋ ከነጻች በኋላ ገላዋን ታጥባ ትገባለች። ፍት.ነገ.አን6 ሠለስቱ ምዕት በድጋሚ «ሐራስ ወትክት ኢትባእ ውስተ ቤተ ክርስቲያን» በማለት መዋዕለ ንጽሕናዋን ያልፈጸመች ወላድና ከደመ ጽጌዋ ያልነጻች ሴት ቤተ መቅደስ እንዳትገባ አዘዋል።

በወር አበባ ላይ ያለች ሴት ወደ ቤተ ክርስቲያን አትግባ ማለት ቤተ ክርስቲያን አትሂድ ማለት አይደለም። ቤተ ክርስቲያን ሄዳ የመጀመሪያውን ቅጽር (አጥር) ከገባች በኋላ በመጠለያና በገረገራ ውስጥ ሆና ትጸልይ፣ ትማር፣ ማንኛውንም መንፈሳዊ ነገር ትከታተል እንጂ ወደ ቤተ መቅደስ ተደፋፍራ አትግባ ማለት ነው።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያስተምርበት ጊዜ ጻፎችና ፈሪሳውያን በምንዝር የተያዘችን ሴት ወደ እርሱ አምጥተው «በመካከልም እርሷን አቁመው መምህር ሆይ ይህች ሴት ስታመነዝር ተገኝታ ተያዘች» ማለታቸው በግልጽ ተጽፏል። ዮሐ8፥1-5 ይልቁንም በቁጥር2 እና 20 ላይ የተጻፉት «ወደ ቤተ መቅደስ ደረሰ» እና «ኢየሱስም በመቅደስ ሲያስተምር» የሚሉት ሐረጎች ይህ ታሪክ የተፈጸመው በቤተ መቅደስ መሆኑን በጉልህ ያሳያሉ።

በዘመነ ኦሪት እንኳን ያመነዘረ ሰው ይቅርና በትዳሩም ቢሆን ሩካቤ የፈጸመ ሰው ዕለቱን ወደ ቤተ መቅደስ መግባት አይችልም ነበር። ታዲያ ይህች ሴት ስታመዝር ተገኝታ ተይዛ ሳለ በቤተ መቅደስ ያውም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት በክስ ለመቆም እንዴት ቻለች?

በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ8 ቁጥር3 እና 20 ላይ እንደተተረጎመው ቤተመቅደስ ሦስት ቅጽር ነበሩት። ስለዚህ ድቀት ያገኘው ማለትም :- በዝሙት የተሰነካከለ፣ ሕልመ ሌሊት ያየ ሰውና በወር አበባ ላይ ያለች ሴት የመጀመሪያውን አጥር ብቻ አልፈው ገብተው ይሳለሙና መባቸውን ሰጥተው፣ ተምረው፣ ሌላም መንፈሳዊ ተግባር አከናውነው ይመለሳሉ። ወደ ውስጥ ግን ዘልቀው መግባት አይችሉም ነበር። ስለዚህ ከላይ ስታመነዝር ተገኝታ የተያዘችውም ሴት የገባችው የመጀመሪያውን አጥር ብቻ ነው። በዚህ ታሪክ





መሠረት በወር አበባ ላይ የሚገኙ ሴቶች ወደ ቤተ መቅደስ መግባት አይፈቀድላቸው እንጂ ከቅጽረ ቤተክርስቲያን ገብተው ጸልየውና ተምረው ወይም ማንኛውም መንፈሳዊ ተግባር አከናውነው መመለስ የሚከለክላቸው የለም።

## ወደ ቤተ መቅደስ ለምን አይገባም?

የወር አበባ ርኩሰት አለመሆኑ ከላይ በሚገባ ተብራርቷል። ታዲያ ርኩሰት ካልሆነ በዚህ ወቅት ሴቶች ወደ ቤተ መቅደስ እንዳይገቡ ሥርዓት የተሠራው ለምን ይሆን? ለዚህ ጥያቄ መልስ ሊሆኑ የሚችሉ ዋናዋና ነጥቦች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው።

1. በወር አበባ ወቅት ድካምና ልዩ ልዩ የሕመም ስሜቶች እንደሚከሰቱ ከላይ በቂ ማብራሪያ ተሰጥቷል። ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ወዲህና ወዲያ ሳይሉና ሳይንቆራጠጡ መንፈሳዊውን ሥርዓተ ጸሎት ማድረስ እንደሚገባ የሚያስረዳ ሥርዓት አላት። ሆኖም በወር አበባ ላይ የሚገኙ ሴቶች በሚሰማቸው ሕመም ምክንያት ጉንበስ ቀና በማለትና በመንቆራጠጥ የሌላውን ጸሎጸኛ ልቡና እንዳያውኩና ራሳቸውም ምቾት እንዳያጡ በማሰብ ከቤተ መቅደስ እንዳይገቡ ተከልክለዋል። በዚህ ዓይነት የሕመም ስሜት ላይ ሆኖ ሕሊናን ሰብስቦ በተረጋጋ መንፈስ መጸለይ እጅግ ያስቸግራል። በእርግጥ በወር አበባ ወቅት ሕመም የማይሰማቸው አንዳንድ ሴቶች መኖራቸው ቢታወቅም ሥርዓት የሚሠራው ብዙኃኑን ከግምት በማስገባት መሆኑን መዘንጋት የለበትም። ስለዚህ በወር አበባ ላይ የሚገኙ ሴቶች በሚሰማቸው ሕመም ምክንያት ተረጋግተው የማይጸልዩ፣ የማያስቀድሱ ...ወዘተ ከሆነ ወደ ቤተ መቅደስ ለምን ይገባሉ? ቤተ ክርስቲያን የጸሎትና የመንፈሳዊ ተግባር ማከናወኛ ቤት ናት እንጂ ሌላ ዓላማ የላትምና።

«በወቀቱ ንጽሕናን ለመጠበቅ ስለሚያዳግት ነበር» የሚሉት አሁን ግን ንጽሕናን ለመጠበቅ ምንም ችግር ስለሌለ ብንገባስ ለማለት እንዲረዳቸው ነው። ምክንያት ሰጪ ራሳቸው ምክንያቱንም አፍራሾች ራሳቸው ናቸው። ወደ ቤተ መቅደስ የማይገባበት ትክክለኛ ምክንያት ግን ከተራ ቁጥር 1 እስከ 7 ባለው በዝርዝር ተጽፏል።

በቀድሞ ጊዜ ንጽሕናን ለመጠበቅ ምቹ ሁኔታ ስላልነበረ ይህ ሥርዓት ተሠራ ማለት ሥርዓቱ የተሠራው ለጊዜው አማራጭ እስኪገኝ ድረስ ብቻ ነበር እንደማለት ይቆጠራል። በተጨማሪም ይህ ሥርዓት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት አልተሠራም ወይም ራሱ መንፈስ ቅዱስም ቢሆን ክብር ይግባውና! መጪውን ጊዜ አያውቅም ወይም የቴክኖሎጂን ዕድገት ከግምት ውስጥ አስገብቶ ሥርዓቱን አልሠራም እንደ ማለት ነው።

በተጨማሪም በዚህ ዘመን እንኳን ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ብንመለከት የዘመኑ ቴክኖሎጂ ያፈራውን በመጠቀም በወር አበባ ጊዜ ከሚከሠት የንጽሕና ጉድለት ለመዳን የሚችሉ ሴቶች ቁጥር እጅግ ጥቂት ነው። አነስተኛ ገቢ ያላቸው ወይም በገጠር አካባቢ የሚኖሩ ሴቶች ኑሮአቸው ከድሮው ጊዜ ባልተለየ መልኩ መሆኑ ይታወቃል። ታዲያ ከላይ በተገለጸው መልኩ ንጽሕናቸውን ለመጠበቅ ለቻሉ ሰዎች ወደ ቤተ መቅደስ መግባት ቢፈቀድ ያልቻሉትስ? የሚል ጥያቄ ማስነሣቱ አያቀርም። ላልቻሉት እንደቀድሞው ቢከለከሉ ደግሞ ቤተክርስቲያን በሀብታምና በድኃ መካከል ልዩነት ፈጥራ የምታስተዳድር ፍትሐዊነት የሌላት ትሆናለች።

ከእኛ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ጋር ኅብረት ያላቸው „እኅት አብያተ ክርስቲያናት ከኛ የሚለዩበት ብዙ ቀኖና እንዳለ የታወቀ ነው። እነርሱ በወር አበባ ወቅት ሴት ልጅ ቤተ





መቅደስ እንዳትገባ ሥርዓት ሠሩም አልሠሩም ከእኛ የሚጠበቀው የራሳችንን አክብሮ መያዝ ነው። በዚህ መልኩ እነርሱን መምሰል ይገባናል ማለት ዐላዋቂነት እንጂ ሥልጣኔ ሊሆን አይችልም።

በልዩ ልዩ ምክንያት ባሕር ማዶ ተሻግሮ ከአገር ርቆ መኖር ያለ ቢሆንም ከሥርዓት መውጣት ግን አይገባም። አንዳንድ ሰዎች ደካማነታቸው፣ የውስጥ ስሜታቸውና እምቅ ክህደታቸው የሚገለጠው ባሕር ሲሻገሩ ነው። የእነዚህ ዓይነት ሰዎች የክህደታቸው ማራገፊያ ወደቦች ደግሞ ሥርዓት ማፍረስ ሥልጣኔና ዘመናዊነት መስሎ የሚታያቸውና ማንነታቸው የጠፋባቸው ሰዎች ናቸው። በምንም ዓይነት ሁኔታና በየትኛውም ቦታ ሆኖ ለሥርዓት ተገዥ መሆን በእጅጉ ይጠቅማል። ስለዚህ «ሴት ልጅ በወር አበባ ላይ ሳለች ወደ መቅደስ አትግባ» የሚለውን ትዕዛዝ አበው በየትኛውም ቦታ ልናከብረው ይገባል።

የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት በሌላ መንፈስ መመልከት ተገቢ አይደለም። በሴቶች ላይ የወር አበባ እንዳለ ሁሉ በወንዶችም ላይ ወደ ቤተ መቅደስ እንዳይገቡ የሚያግዳቸው ዝንየት (ሕልመ ሌሊት) የሚባል ምክንያት አለባቸው። ስለዚህ ይህ ሥርዓት ሴቶችን ለመጨቆን ወይም ከወንዶች ለማሳነስ ሆን ተብሎ የተሠራ ባለ መሆኑ ከመብትና ከጾታ እኩልነት አንጻር ማየት ፖለቲከኛ እንጂ ሃይማኖተኛ ሊያደርገን አይችልም።